ሚያዝያ 18 | 2017 ዓ.ም



# ዘሪቱ እንደምን ተጽናናች?

የደራው መጽሔት

# በእርሱ ቁስል

## እኛ ተፈወስን

ትንቢተ ኢሳያስ 53፡3




ፀሐይ
አትጠልቅም
www.yederaw.com

# ማውጫ

ምስሉን ሲጫኑት ወደ ፈለጉት ገጽ ይወስዶታል




ካሜራም ባይኖር ለግሱ 8




የሰሞኑን ውዝግብ 11



የእግዱ ጣጣ 15




ታላቁ ሩጫ 19

# ማውጫ





ታላቁ ፍጥጫ 26







የደራው ሰሌዳ 32





ተስፋ አስቆራጭ ሰዎች 28


ዘሪቱ እንደምን ተጽናናች? 33






አዲስ ቅኔ 42


www.yederaw.com



# የደራው

1ኛ ዓመት | ሚያዝያ 18 | ቁጥር ሰባት
+251919474444
www.yederaw.com
Magazine@Yederaw.com
አዲስ አበባ,ኢትዮጵያ

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ያፌት ገ/ህይወት(ምትኩ)

**ዋና አዘጋጅ**
ሰለሞን ከበደ
solomon@Yederaw.com

**ም/ዋና አዘጋጅ**
አቤኔዘር ወርቁ

**ሪፖርተሮች**
አሌኒ ግዛው
አያንቱ ሁንዴ

**ፎቶግራፈሮች**
ዳንኤል አበበ
ያሬድ ግስላ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
አብርሃም ቦሪስ

**ማርኬቲንግ**
ልዕልት በላይነህ
marketing@Yederaw.com
+251919474444

**ቴክኖሎጂ ዳይሬክተር**
ሱራፌል ተፈሪ

**ክሬቲቭ ዳይሬክተር**
ያፌት ገ/ህይወት

**ጸሐፊ**
ምስጢር ጌታቸው

# ካሜራም ባይኖር
# ለግሱ

በዓል በመጣ ቁጥር ተቋማት እና ግለሰቦች ለአቅመ ደካማዎች እና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚኖሩ ማህበረሰቦች ዘይት ፣ ዱቄት ፣ ዶሮ ሽንኩር እና ወዘተ... ለዚህ ያህል ሰዎች እርዳታ አደረጉ የሚሉ ዜናዎችን በመገናኛ ብዙሀን ሰፊ ሽፋን ሲሰጣቸው እንመለከታለን።

መረዳዳት እና ያለውን ተካፍሎ መኖር ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው። መደጋገፍ መረዳዳት ዘላቂ አብሮነት ያጠናክራል። አብሮነት፣ መደጋገፍ ፣ እና መረዳዳት የእኛ የኢትዮጲያዊያን እሴቶች ናቸው።

እነዚህ  የኢትዮጵያዊያን እሴቶች እየተበረዘ እና መልካቸው እየተቀየረ የአንድ ሰሞን የወሬ ማድመቂያ መሆን ከጀመሩ ዋል አደር ብለዋል። ተቋማት በዓል ጠብቀው ከብዙህ የዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ነዋሪዎች መካከል ለጥቂቶችን የአይነት ድጋፍ በማድረግ የገፅታ መገንቢያቸው አድርገውታል።

በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ ዜጎችን ማቋቋም እና መደገፍ የሁሉም ማህበራዊ ሀላፊነት ነው። በመሆኑም እነዚህን ዜጎች ወቅት ጠብቆ ሳይሆን በቋሚነት የራሱ መመሪያ ተዘጋጅቶለት በህጋዊ እና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሰራር መደገፍ የተቋማት ግዴታ ነው።

የነድያን እርዳታ እና የበጎ ፈቃድ ስራዎች  ዘላቂ አብሮነትን ፣ እና ማህበራዊ ትስስርን ያጠናክራሉ።

በመሆኑም ሰው በአመት አንዴ የሚመጣ በዓልን ጠብቆ የሚመገብ እና የሚለብስ ባለመሆኑ ተቋማትም ሆኑ ግለሰቦች እነዚህ ዜጎች በቋሚነት በመደገፍ ማህበራዊ ግዴታቸውን በመወጣት  ወገንተኝነታቸውን እና አብሮነታቸውን ማጠናከር አለባቸው።

አንድ ተቋም አንድ ቤተሰብ በቋሚነት ቢደግፍ ፤ ትልቅ እረፍት ነው።

ለስራ ከተነሳን " ፀ ሐ ይ  አ ት ጠ ል ቅ ም ! ''

የደራው ዝግጅት ክፍል
መልካም የዳግም ትንሳዔ በዓል እንዲሆንላችሁ ይመኛል!

የአዘጋጆቹ መልዕክት!

የደራው
መጽሔት
ፀሐይ አትጠልቅም!

AD

# ህልሞት ሪሳካ ነው!

ህልሞት ሪሳካ ነው!

UTOPIA
Making Dreams Come True

የቤንዚል ወጪ ዐ ብር ሆነ ! የኤሌክትሪክ መኪና ኢቮሊሽን ይቀላቀሉ !



ዩቶፕያ ቴክኖሎጂ
+251 975 80 80 80
+251 976 80 80 80
8022
ugmfund.com

የኤሌክትሪክ መኪና በመንዳቶ ! በ15 አመት ለነዳጅና እና ለዘይት የሚያወጡትንከ 2 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ያትርፉ !

# የሰሞኑን ውዝግብ

## “ ለውይይት በራችንን ከፍተን እየጠበቅን ነው “ - ገቢዎች ቢሮ

## “ ቀን እና ቦታው ከተነገረን ህጋዊነታችንን የሚያረጋግጥ ዶክመንት ይዘን ለመነጋገር ዝግጁ ነን “ - ማኀበራቱ

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በኢትዮጵያ የሂሳብ እና የኦዲት ቦርድ ፈቃድ ከተሰጣቸው 863 የሂሳብ ባለሙሞያዎችና ኦዲተሮች ያቀረቡት የሂሳብ ሪፖርት በማሳነስና በመሰወር የቀረበ ነው ሲል ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ፍቃድ መንጠቅ የደረሰ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ጠይቋል።

“ የገቢ ግብርን በማሳነስና በመሰወር የተሳሳተ የሂሳብ ሪፖርት አቅርበውልኛል እርምጃ ይወሰድባቸው “ ብሎ በሚዲያ ያስተላለፈው መረጃ የኦዲተርነት ሙያን ከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ መክተቱን የሂሳብና የኦዲተሮች ማህበራት ተናግረዋል።

በቅርቡ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ከወንኩት ባለው የቅድመ ኦዲት ስራ “ ባለፈው ዓመት ብቻ 36,729 የታክስ መዝገቦች ገቢ በማሳነስና በመሰወር የሚቀርቡ መሆናቸውን ደርሼበታለሁ “ ብሏል።

በዚህም መሰረት በኢትዮጵያ የሂሳብ እና የኦዲት ቦርድ ፈቃድ ከተሰጣቸው 863 የሂሳብ ባለሙሞያዎችና ኦዲተሮች 824ቱ ባለሞያዎች ያቀረቡት የሂሳብ ሪፖርት በማሳነስና በመሰወር የቀረበ በመሆኑ፤ በቦርዱ ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ፍቃድ መንጠቅ የደረሰ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ቢሮው ጠይቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ

ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
REVENUES BUREAU

ይህን ተከትሎ 3 የሂሳብና የኦዲተሮች ማኀበራት ተፈፀመ የተባለው ስህተት በቦርዱ ሳይረጋገጥ መረጃው በሚዲያ መተላለፉ አግባብነት የሌለውና ሙያውንም ኪሳራ ውስጥ የከተተ ነው ሲሉ መግለጫ አውጥተዋል።

በመግለጫቸውም “ ባለሙያዎቹ ይቀጡልኝ “ የሚለው ጥያቄ ላይ ምንም ቅሬታ እንደሌላቸው ጠቅሰው ይሁንና በሚዲያ የተላለፈበት አግባብ አሳሳች የነበረ በመሆኑ መረጃው ከሚዲያዎችና መረጃ ቋቶች ላይ እንዲወርድ ጠይቀዋል።

ይህንንኑ ጥያቄያቸውን ማቅረባቸውንና በጉዳዩ ዙሪያ ለመነጋገር የገቢዎች ቢሮን በደብዳቤ መጠየቃቸውን የገለጹት የኢትዮጵያ የሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ማህበር፣ የውጭ ኦዲተሮች ማህበርና የአካውንቲንግ ሶሳይቲ ኦፍ ኢትዮጵያ ማህበር ናቸው።

በጉዳዩ ላይ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ምን ምላሽ ሰጠ ?

በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ለውይይት ለመቀመጥ የማህበራቱን ህጋዊ እውቅና እና የአባላት ዝርዝር በህጋዊ መንገድ እንዲቀርብለት ጠይቋል።

የቢሮው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው አቶ ሰውነት አየለ ለማኀበራቱ አመራሮች በስልክ በመደወል ህጋዊ እውቅናቸውን እንዲያቀርቡ ነግረናል ያሉ ሲሆን ለውይይት በራችንን ከፍተን እየጠበቅን ነው ሲሉ ለሸገር ኤፍ ኤም ተናግረዋል።

ቢሮው 863 የሂሳብ ባለሙያዎች ይቀጡልኝ ሲል ለኢትዮጵያ የሂሳብና የኦዲት ቦርድ ማቅረቡን ተከትሎ በሚዲያ የወጣው መግለጫ በተመለከተ፣ አቶ ሰውነት በስም ዝርዝር የተነሳ የለም በማለት የተሰራው ስራ በአዋጅ በተቀመጠው መሰረት እንደሆነ አስረድተዋል።

አክለውም “ እስካሁን በስም ዝርዝር ያወጣነው ነገር የለም ያሉ ሲሆን 490 የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጥልን 333 ደግሞ ፈቃዳቸው ይሰረዝ 39ኙ እውቅና ይሰጣቸው ያልነው በደፈናው ነው “ ብለዋል።

ማጣራቱ ከተጠናቀቀ እና ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በስም ዝርዝር ይፋ እንደሚደረግም አቶ ሰውነት አየለ ተናግረዋል።

## ማኅበራቱ በቢሮው ምላሽ ላይ የሚያነሱት ጥያቄ ምንድነው ?

ማኅበራቱ“በደብዳቤለጠየቅነውጥያቄበደብዳቤምላሽአልተሰጠንም “ ያሉ ሲሆን በስልክ ቅድመ ሁኔታውን እንዲያሟሉ እንደተነገራቸው እና መቼ እንደሚወያዩ ቀጠሮ እንዳልተሰጣቸው ለሸገር ኤፍ ኤም ገልፀዋል።

የውጪ ኦዲተሮች ማህበር ስራ አስኪያጅ አቶ ሚሊዮን ማሞ ለሁለቱ ማህበራት ፕሬዚዳንቶች“እውቅናንእናየአባላትንዝርዝርበህጋዊመንገድ አረጋግጣችሁ አምጡ “ የሚል ቅድመ ሁኔታ በስልክ እንደተነገራቸው አረጋግጠዋል።

የማህበራቱን እውቅና ማረጋገጫ ማቅረብ እንደሚቻል “ የማህበራቱን አባላት ዝርዝር ግን ይዞ መቅረብ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም “ ብለዋል። በተጨማሪ አቶ ሚሊዮን “ ‘ህጋዊነታችሁን የሚያረጋግጥ ዶክመንት በዚህ ቀን ይዛችሁ ኑ እና እንወያይ ‘ የሚል ሃሳብ አልተሰጠም “ ያሉ ሲሆን “ በደብዳቤም በፅሁፍም ምንም ነገር አልተባለም “ ሲሉ ተናግረዋል። አቶ ሚሊዮን፥ ቀን እና ቦታው ከተነገራቸው ማኅበራቱ ህጋዊነታቸውን የሚያረጋግጥ ዶክመንት ይዘው ለመነጋገር ዝግጁ መሆናቸውን ሸገር ኤፍ ኤም ገልጿል።




የድል
ዋዜማ
ትጋት ነው!



# “አግራ” በዩኤስኤአይዲ መቋረጥ 40 ሚሊዮን ዶላር አጣ

የአፍሪካ አረንጓዴ አብዮት ህብረት (AGRA) የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ በወሰዱት የእርዳታ ቅነሳ ምክንያት 40 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት የገንዘብ ድጋፍ ማጣቱን አስታውቋል።

በኬንያ መቀመጫውን ያደረገዉ አግራ በኢትዮጵያ ጨምሮ በ12 የአፍሪካ አገራት ውስጥ ከትናንሽ አርሶ አደሮች ጋር በመተባበር የግብርናና ልምዶችን ለማሻሻል፣ ገቢን ለማሳደግ እና ዘላቂ ልማትን ለማበረታታት የሚሰራ ግዙፍ ግብረሰናይ ተቋም ነው።

ድርጅቱ እንደገለፀዉ ከ የዩኤስኤአይዲ የሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ መቋረጥ ቀደም ሲል የተጀመሩ ሥራዎችን እየጎዳ እንደሚገኝ ጠቁሟል።

የአግራ ፕሬዝዳንት አሊስ ሩህዌዛ እንደተናገሩት ሌሎች የአውሮፓ አገራት ለጋሾችም የገንዘብ ድጋፋቸውን እየቀነሱ መሆኑን ።

ይህ የ 40 ሚሊዮን ዶላር ኪሳራ አግራ ከ ዩኤስኤአይዲ ሊያገኘው ከታቀደው 100 ሚሊዮን ዶላር የእርዳታ አካል እንደነበር ገልጿል።

በተመሳሳይ በዚህ ሳምንት የተባበሩት መንግስታት የዓለም ምግብ ፕሮግራም በኢትዮጵያ በቂ የገንዘብ ድጋፍ ባለመኖሩ 650,000 የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ያለባቸውን ሴቶችና ህጻናት እርዳታ ሊያቋርጥ እንደሚችል አስታውቋል።

#cnp

ለበዓል የወጣ
ታላቅ ቅናሽ!

90 ካሬ በ5,778,000 ብር
130 ካሬ በ8,346,000 ብር

Temer
PROPERTIES



ቴምር ሪል እስቴት
ሳር ቤት ላይ

0912685310


AD
የደራው
በቅርብ ቀን




# 25ኛ ዓመት ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አለም አቀፍ 10ኪ.ሜ. ህዳር 14

የብር ኢዮቤልዩ ላይ የደረሰው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አለም አቀፍ 10ኪ.ሜ. ሊከናወን ሰባት ወራት ቀሩት። ህዳር 16 ቀን 1994ዓ.ም. ጅማሮውን ያደረገው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በቀጣይ ህዳር 14 ቀን 2018ዓ.ም. 25ኛ ዙር ውድድሩን ያከናውናል።


ከአፍሪካ ትልቁ የ10ኪ.ሜ. የጎዳና ላይ ውድድር የሆነው ዝግጅቱ ባለፉት 24 የውድድር ዓመታት ወደ 760ሺህ አካባቢ ሰው በ10ኪ.ሜ. ውድድሩ ላይ አሳትፏል።

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የዘንድሮ ውድድር በተጠናቀቀ ማግስት የ25ኛ ዓመት ክብረበዓሉን አስመልክቶ ለቀጣዩ ዓመት 500 ቀዳሚ ተሳታፊዎች በነጻ ምዝገባ ያከናወነ መሆኑ ይታወሳል። ለሌሎች የውድድሩ ተሳታፊዎች ምዝገባ ሐምሌ ወር ላይ እንደሚከናወን ተገልጿል።

“25ኛ ዓመታችንን አብረውን በመሆን ካበረቱን ሁሉ ጋር ለማክበር ተዘጋጅተናል ፤ ደስታችንን ከራሳችን ለመጀመር በዚህ እሁድ ኬንያ በሚደረገው ኤልዶሬት ማራቶን ላይ ተሳትፈን እና ሩጫችንን አስተዋውቀን እንመለሳለን።” ያሉት የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ስራ አስኪያጅ ዳግማዊት አማረ “ከወዲሁ ከሩጫችን ጋር የተያያዘ የተሳታፊዎቻችንን ልዩ ልዩ ታሪኮች እና ገጠመኞች መሰብሰብ ስለጀመርን በማህበራዊ ሚድያ ገጾቻችን ላይ ቢነገር የሚሉትን ትውስታቸውን ያካፍሉን” ሲሉ ለተሳታፊዎች ጥሪ አቅርበዋል።

ከ24 ዓመታት በፊት ውድድሩ ሲጀመር ኃይሌ ገብረስላሴ እና ብርሃኔ አደሬ የመጀመሪያውን ዓመት ውድድር ያሸነፉ አትሌቶች ሲሆኑ ፤ በዘንድሮ ውድድር ላይ ወጣቶቹ አትሌቶች ቢንያም መሃሪ እና አሳየች አይቸው ማሸነፋቸው ይታወሳል።


"ተስፋችንን እንይ"




# የታክሲ እና የቤንዚል ሰልፍ ሰልችቶታል?

እንግዲያውስ ድርጅታችን ዩቶፕያ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን “ዩቶፕያ ግሪን ፈንድ በመተግበር በ5 አመት 10,000 አባላትን የመኪና ባለቤት ያደርጋል!

እንዴት?

1. በየመኪና ሊዝ ከቅድመ ክፍያ ጋር ፓኬጅ

ቅድሚያ ከ30% ማለትም 897,000 ብር ጀምሮ በመክፈል መኪናውን በ 3ወር ጊዜ ይረከባሉ !

ወይም

2. በየመኪና ሊዝ ከእቁብ ጋር ፓኬጅ

በቀን ከ292 ብር ጀምሮ በመቆጠብ በየ4ወሩ ከ100 እስከ 600 ደንበኞች በሚወጣ የመኪና እጣ ከ3 ወር እስከ 3 አመት በሚሆን ጊዜ የመኪና ባለቤት የሚሆኑበትን እድል እመቻችተናል።

- የረጅም ጊዜ ዋስትና ፣ ፈጣን የቻርጂንግ ሰርቪስ፣ የተሟላ ጥገና እና መለዋወጫ አመቻችቷል፡፡

- የመመዝገቢያ ክፍያ በግል 89,700ብር ወይም በጋራ ለ3 በመሆን 29,900 ብር

**ዩቶፕያ ግሪን ሞቢሊቲን ይቀላቀሉ !**
**በ www.ugmfund.com ፈጥነው ይመዝገቡ !**
**ይጫኑት ወደ ድረ-ገጹ ይወስዶታል**

**አድራሻ :-**
**ቅ/ር 1. ከአምባሳደር ሲኒማ ፊትለፊት ከመከላከያ መስርያ ቤት አጠገብ በሚገኘው *TT* ሲኖስ ህንፃ ምድር ላይ !**
**ቅ/ር 2. ቦሌ መድሀኒያለም ሞል 7ኛ ፎቅ**

**ኮል ሴንተር : - 8022**

**ሞባይል :- 09 75 80 80 80 / 09 76 80 80 80 /**
**09 45 84 44 44 / 09 45 94 44 44**


AD



# የደራው ላይ ያስተዋውቁ ገበያዎን ያድሩ!

ያግኙን : 0919474444




**አርቲስቶች ፣ ድምፃዉያን ፣ ጋዜጠኞች እና ቲክቶከሮች የሚሳተፉበት ደማቅ ስፖርታዊ ዉድድር ሊደረግ ቀን ተቆርጦለታል**

**ሚያዝያ 23 ለዋንጫ የጥሎ ማለፍ ዉድድር የሚደረግ ሲሆን ሚያዝያ 26 ደግሞ የፍፃሜዉ የዋንጫ ጨዋታ ይደረጋል።**

**ትኬቱን ከቴሌ ብር ላይ ከዛሬ ጀምሮ መግዛት የሚቻል ሲሆን ከትኬት ሽያጭ የሚገኘዉም ገቢ ለመቄዶንያ የአረጋዉያን እና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል የሚዉል ይሆናል።**

**ውድድሩ ከልደታ ቤተክርስቲያን ጀርባ በሚገኘው ብሪሞ ሜዳ ይደረጋል።**







## ተስፋ የሚያስቆርጧችሁ ሰዎች

በአውራ ጎዳና ላይ አበባ እየዞረ የሚሸጥ አንድ ድሃ ልጅ ነበር። አንድ ቀን አንድ አዛውንት አስቁመው እንዲህ አሉት።

“እንዲህ ባለ ሥራ በበዛበትና አደገኛ መንገድ ላይ ለምንድን ነው አበባ የምትሸጠው?”
ልጁ መለሰ። “ቤተሰቦቼ ድሆች ናቸው የትምህርት ቤት ወጪዬን መሸፈን አይችሉም።”
አዛውንቱ አሉት። “ግን አንተ ትንሽ ልጅ፣ የምታደርገው ነገር ስህተት ነው። በዋናው መንገድ ላይ በመሮጥ በጣም ትልቅ አደጋ ውስጥ እየገባህ ነው። በመኪና ልትገጭ እንደምትችል ታውቃለህ?”
ልጁ በሹክሹክታ እንዲህ አለ። “ወደ ትምህርት ቤት መመለስ እንድችል ገንዘብ ማግኘት ብቻ ነው የምፈልገው።”
አዛውንቱ በቁጣ መለሱ። “ግን ህይወትህ ከትምህርት የበለጠ አስፈላጊ ነው። ትምህርት ቤት ያልገቡ ነገር ግን ታላቅ ሰዎች የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ። የተማርክ ለመሆን ስትል ልትሞት ነው? አሁን ስማኝ፣ በመኪና ከተገጨህ ትሞታለህ፣ ከሞትክ ደግሞ ትምህርት የለም። ገባህ?”
ከዚያም አዛውንቱ አከሉ።

“ትምህርት የስኬት ቁልፍ አይደለም። ህይወትህን ለእሱ አደጋ ላይ አትጣል።”
ድሃው ልጅ አዛውንቱ ርቀው ቢሄዱም ቃላቶቻቸውን እያሰላሰለ ቀረ። ለብዙ ቀናት፣ ደጋግሞ ካሰበ በኋላ ዳግመኛ አበባ ላለመሸጥ ለራሱ ቃል ገባ።
ከአስራ አምስት ዓመታት በኋላ፣ ያ ድሃ ልጅ ወደ ወጣትነት አድጎ ምንም የገቢ ምንጭ ሳይኖረው ይበልጥ ድሃ ሆነ። አንድ ቀን አንድ አዛውንት አግኝቶ ለመናቸው።

“ይቅርታ ጌታዬ፣ ጥቂት ሳንቲም ሊሰጡኝ ይችላሉ?”
አዛውንቱ በቁጣ ተናገሩ። “አረ! ራስህን ከልመና ለማውጣት ለምን አልተማርክም?”
ወጣቱ መለሰ። “ወላጆቼ ድሆች ነበሩ እና ወደ ትምህርት ቤት ሊልኩኝ አልቻሉም።”

አዛውንቱ በቁጣ እንዲህ አሉ።

“ወላጆችህን አትውቀስ። የትምህርትን አስፈላጊነት ስለሚያውቁ ብዙ ልጆች የትምህርት ቤት ወጪያቸውን ለመሸፈን በልጅነታቸው ጠንክረው ሰርተዋል ህይወታቸውንም አደጋ ላይ ጥለዋል። አንተ ግን ምንም አላደረግክም፣ ስለዚህ ሁሉም ያንተ ጥፋት ነው!”
ወጣቱ በአዛውንቱ ቃላት ልቡ ተሰብረ፤ ተከፋ። ከምንም በላይ እንዲህ የሚቆጣው ከአስራ አምስት ዓመት በፊት ያገኘው ያው ራሱ አዛውንት መሆኑን ሲያውቅ ይበልጥ አዘነ።

ልታደርጓቸው የምትፈልጓቸውን ነገሮች እንዳታደርጉ ተስፋ ሊያስቆርጧችሁ የሚሞክሩ ሰዎችን ምን ያህል ጊዜ ትሰማላችሁ?

የሌሎች አስተያየት ምን ያህል ጊዜ እንዲቆጣጠራችሁ ትፈቅዳላችሁ?

ህልማችሁን ከማሳደድ ተስፋ የሚያስቆርጧችሁ ሰዎች፣ ህልማችሁን ባለማሳካታችሁ የሚወቅሷችሁ እነዚሁ ሰዎች መሆናቸውን ታውቃላችሁ? ስራችሁን ለመፍረድ ፈጣኖች ናቸው፣ነገር ግን ገንዘብ ሲያጥርባችሁ አይረዷችሁም። እጣ ፈንታችሁን ራሳችሁ ተቆጣጠሩ። በራሳችሁ እመኑ። ተስፋ ሊያስቆርጧችሁ የሚሞክሩትን ችላ በሉ። ማን መሆን እንደምትፈልጉ የምትወስኑት እናንተ ናችሁ የሌሎች ሰዎች ወደ ኋላ ጎታች አስተያየትን ልትቀበሉ አይገባም።

ጽኑ፤ በትኩረት ስሩ።
እግዚአብሔር ይባርካችሁ።
እወዳችኋለሁ ያላችሁ “ተዋናይ” ነው



በነፃ
ዲጂታል
ጊፍት ካርድ
ለወዳጅ ፣ ለቤተሰቦ ፣ ለዘመዶ ይላኩ
Meskerem Getu
TESFA
ምስሉን ይጫኑ

# የደራው ሰሌዳ



Cargo
AWASH




Lela fashion
Stay Home
Place Your order & get it
in less than 15 days
+251941521102




Temer
PROPERTIES
ለበዓል የወጣ
ታላቅ ቅናሽ!
90 ካሬ በ5,778,000 ብር
130 ካሬ በ8,346,000 ብር
ቴምር ሪል እስቴት
ሳር ቤት ላይ
0912685310

በተመስገን ሉካሬ
(የሐጌ ልጅ)

# ዘሪቱ እንደምን ተጽናናች?

ከያኒት እና የቀድሞ ድምፃዊት የአሁንዋ ዘማሪት ዘሪቱ ከበደ የመጣችበትን የሕይወት መሰናክል እና ስኬቶቿን በግጥም የመሰነድ በዜማም የመናገር ልማድ አላት።የደረሰባትን እና የደረሰላትን በልቧ አውርታው አታበቃም።የሀሴት አጋጣሚዎቿን ለራሷ ብቻ አታወራም ለኛም ትነግረናለች፡፡ጉዞዋ ሁሉ የተገለጠ ነው፡፡

ብላቴና ሳለች ጀምሮ ሙዚቃ ምን እንደሆነ ታውቃለች፡፡የምናብ ቅዠት የሚመስለውን ረቂቅ ጥበብ ወደ ገሃዱ ለመተርጎም ከገበያ ግብግብ ተላቃ ራሷን ጥበብን ብቻ ትሰጠናለች፡፡

አውቃው ብቻ ዝም አትልም የህዝብን ልብ ለማሸነፍ ሰዎችን ምን እንደ ሚሏትም ታዳምጣለች ምላሽ የመስማትም ክህሎት የልጅነት ክሎቷም ጭምር ነበር።አንድ አንድ ቤተሰብ ልጅ ወደ ጥበቡ ዓለም ሲቀላለቀል ይቃወማል አይስማማም የዘሪቱ ቤተሰብ ግን ይህንን አላደረጉም የሙዚቃ ወዳጅ ስለ ነበሩ ድጋፍ ከቤትም አግኝታለች፡፡



ዘሪቱ በሰከኑ ዜማዎች ሰዎችን በሚያንፁ መንፈሳዊ ዳራ ያላቸው ግጥሞች ቦሌ ሬድዋን ህንጻ በነበረው የኤልያስ መልካ ዓለም በገና ስቱዲዮ ከኤልያስ ጋር የተዋህዶ መልክ የሆነ አልበም ሰጥታናለች።
ኤልያስ እና ዘሪቱ በፍፁም መግባባት እና ተዋህዶ የሰሩት "ዘሪቱ" የተሰኘው አልበም የተሰራው በአንድ አመት ከስድት ወር ጊዜ ወስጥ ሲሆን በአልበሙ ከተካተቱት ሙዚቃዎች "ኦ-ምን አለፋኝ" የተሰነው ተጠቃሽ ነው፡፡

"ኦ-ምን አለፋኝ መልሱ ከጠፋኝ
እሱ አይሳሳት ሁሉን በምክንየት
የእኔም ዓይን አይቷል እሱ ያበሬው
ሰሪ አይበልጥም ወይ ኦ- ከተሰራው"

...ኦ- በራሱ የዚህን ዓለም አድካሚነቷ በሚስጥር ቋንቋ ይናገራል ብትደክም ብትለፋ ምን አመጣለሁ የዚህ ሁሉ አስተካካይ "ዳሩ" ነው በዚህ በኩል በሁለት አለም ግፊት ጉዞ ውስጥ የሚናኝ ተመጣጣኝ ያልሆነ ቅጡን ያጣ ነገር ይታያል፡፡ ለለፋው ጥሩ እትዲገጥመው እና ላለው እንዲሁ ያካፍል ዘንድ በመመኘት በቅን ቋንቋ ትገልፃለች፡፡

ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ስትመላለስ ስትመላለስ ከበለጠው ላይ በልጣ መተናነስ በጨዋ ማንነት ተላብሳ በሰከቱ ማነቶቿ ጋር ከሰሞኑ በፋሲካ እለት "ማፅናናትህ" የተሰኘ ግማሽ(Ep) (ኤክስቴንድድ ፔሌይ) አልበም አድርሳለች በላይብ ፐርፎርፋንስ ቮይስ እና ሪከዲንግ ሚክስ እና ማስተር በብዞ መልክ የተሳካለት ነው፡፡




የግጥም ክብደትነቱ ከተሸከመው ዜማው ጋር ተቆራኝቶ በስሜት እና በውስጣዊ መነካት የተወለዱ በብዙ ወጀብ የተሞላ ግን በተረጋጋ ቅኝት የተዋቡ ዝማሬዎችን አድርሳለች፡፡

“ገረመኝ  ችሎታህ የማጽናናትህ- የማጽናናትህ፤
ደነቀኝ ችሎታህ የማጽናናህ - የማጽናናትህ፤
------------------------------------------------------------
ተሰብሬ ነበር  እንደማልሆን ሆኜ፣
የሚጠላኝን ክስ ትርክቱን አምኜ፤
የከመረብኝን የበደል ድሪቶ፣
ብርሃንህ ገፈፈው ያንተን አስረድቶ”፡፡

ብዞዎቻችን ደረሰብን ላልነው ስብራት ጠጋኝ ለመፈለግ ስጋ የለበሰን ሰው እንሻለን ካጣን ደሞ ይበልጥ እንረበሻለን ፤ ዘሪቱ ግን በልብ ጥንካሬዋ ከፊቱ ሆና በፀፀት እና በንስሃ በመማፀን ጭምር በርህራሄ ሁሉን በሚያውቀው ፈተናን አሻጋሪው ጌታ እግር ስር ትሆናለች፡፡ከመታመም በኋላ መዳን አለ ፥ ከሃዘን በኋላ መፅናናት ከዛም ደስታ አለ ግን እሱ በሰው ሳይሆን በጌታ እጅ ነው እርሱ ዘንድ መጽናናት አለ፡፡
ሌላኛው ደግሞ “በፀጋው” የተሰኘው ነው በዚህ መዝሙር ጥያቄ ትጠይቃለች በገባት ልክ ትመልሳለች ፀጋ የቱ ጋር ነው? ምን ድን ነው ፀጋ? ሙግቷ ሁሉ ከራስ ወቀሳ ጋር የነፍስ ጥያቄዋን አዳብላ ትገልጣለች፡፡መዳረሻው “ኢየሱስ ክርስቶስ” መሆኑን ታስረዳለች፡፡

“የራሱን ጽድቅ ላቆመ
ደህና ነኝ ለሚለው ሰው፣
ጸጋው ምኑ ነው?
ምህረቱስ መች ገብቶት ሊያደንቀው፤
ልምምዱ ላስመሰካው
ሥርዐት መፈጸሙ፣
ጸጋው ምኑ ነው?
ኀጢአቱስ መች ገብቶት ሊጠላው።

---------------------------------------------

ያለም ኀጢአተኞች እንኳን ደስ ያላችሁ፣
ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቷል ሊድናችሁ፤
የዓለም ኀጢአተኞች እንደኔ ያላችሁ፣
ኢየሱስ ያድናል በእርሱ ተስፋ አላችሁ።

--------------------------------------------------

ብለው ብለው ልችለው - ሕጉን ልተገብረው፣
ታገልሁ ልሠራ- የሱን ጽድቅ መስፈርት ልደርሰው፤
ብለው ብለው ልሆነው- ሰው መሆንን እንዳለው፣
ተገኘሁ እዛው- ከክብሩ ጎድዬ ሙት ሆኜ።”

ያለምንም መስፈርት ለወደደን መተላለፋችን ሁሉ ይቅር የሚለን ጉድፋችንን የሚሸከመው ለማንፃት ሌት-ቀን የማይደክመው ጌታ ኢየሱስን ትጣራለች።ለእኔ እንደ ደረሰልኝ ለእናተም በፀጋው ይጎብኛችሁ ነፃነቴን እንዳወጅኩ ነፃነታችሁን ይጋባብኝ የሚል መልዕክትን አንግባ በፍፁም ርዕራሄ እና ፍቅር ትለምናለች።

## ትናትና ዛሬ

ትናትናን በዛሬ መነፅር እየተመለከተች የጥፋተኝነት ስሜት ውስጥ ሆና፤በተሰጠኝ የነፃ ፍቃድ ባልተገባ መንገድ ስጋዬን ሳደክመው እና ጽድቅን ለማግኘት ስትዳክር ፣ ከብርሃን ጋር ቁርኝነት ለመፍጠር ፣ ለመዳን የዓለምን ብልጭልጭ ለመጣል ብዙ ስዳክር ቆየሁ የምትለን ዘሪቱ ያንን ለማስታወስ ለዛሬ መዳን መልክት ይሁነኝ ብላ እንዲህ ትለናለች።

ግን አለፈ ትናንት ላልመለስበት፣
አየሱስ አገኘኝ በማይጥለው ምህረት፤
ዛሬ እኔ ደህና እረፍት ያገኘሁ ሰው፣
እግዚአብሔር ይመስገን ይህን የደረገው
-----------------------------------------------------------
ስለተገዛሁኝ ለእርሱ - ሳልወደው ለወደደኝ፣
በዓለም የማይገኘውን - ሰላሙን አወረሰኝ፤
ስለተገዛሁኝ ለእርሱ - በፍቅሩ ለጣመነደኝ፣
አሮጌው ነገር አለፈ - አዲስ ሰው አደረገኝ።

"ማጽናናትህ" በውስጡ ብዙ ተወዳጅ እና የሚያንፁ ዝማሬዎች አሉት ሰክኖ መስማትን ይሻል እና ዘሪቱ የተስፋን፣የእምነትን፣ እና የፍቅርን ዘር በለመለመው መስክ ዘርታለች ማጨድ የኛ ፋንታ ነው፡፡




ዘሪቱ
ማፅናናትህ
LIVE ALBUM
ZERITU KEBEDE
MATSNANATIH
Drum: Andinet Kebede
Bass: Amanuel Wolde
Lead guitar: Bereket Demeke
Acoustic guitar: Yonathan Dawit
Keys I: Amanuel Alemayehu
Keys II: Illasha Fekadu
Backing vocals:
Addis Alessa
Barnabas Aklile
Bekkem Derrese
Bethlehem Alessa
Christina Muluken
Meti Abera
Music production: Illasha Fekadu
Recording: Abegasu K. Shiota and Elshaday Getahun
Mixing and mastering: Abegasu Kibrework Shiota
1. ትናንትና፡ዛሬ Tinant Ena Zare (Live)
2. ጸጋው Tsegaw (Live)
3. በዛ Bezza (Live)
4. እጄን፡ይዘህ፡ምራኝ Ejen Yizeh Miragn (Live)
5. ና፡ጌታ፡ሆይ Na Geta Hoy (Live)
6. ማጽናናትህ Matsnanatih (Live)
MUSIC
Spotify
music
Music
pandora
© Zeritu Kebede / Matsnanatih 2025. All rights of the producer and the owner of the work reproduced are reserved





መቄዶንያ 8161
ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ
ታላቅ የገቢ ማሰባሰብያ የቀጥታ ስርጭት
Seifu ON ebs YOUTUBE
& Zelle
ACC 240-938-2992
gofundme
MEKEDONIA-HELP US BUILD HOME FOR THE HOMELESS
8161
coop



በታላቅ ድምፅም
እንዲህ ብለው ዘመሩ፤
**‘የታረደው በግ ኀይልና**
**ባለጠግነት፣ ጥበብና ብርታት፣**
**ክብርና ሞገስ፣ ምስጋናም**
ሊቀበል ይገባዋል።’

ራእይ 5፥12






ምስሉን በመጫን
መዝሙሩን ማድመጥ
ይችላሉ




ምስሉን በመጫን
መዝሙሩን ማድመጥ
ይችላሉ




ምስሉን በመጫን
መዝሙሩን ማድመጥ
ይችላሉ

pictures : zeritu social media pages


Bored
Cellphone
Addis Ababa


9262
Radio
የሙዚቃና የሬድዮ ዝግጅት
ያለምንም ኢንተርኔት
ቡሁሉም ዓይነት ስልክ
ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም
HOPE
ENTERTAINMENT
taem
ጣዕም
በሁሉም የማህበራዊ ሚዲያዎች
በድምጽ እና በቪዲዮ አማራጭ
አስተማሪ እና አዝናኝ ታሪኮች
እንዲሁም 24/7 በጥራት የሚደመጥ
በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዲጂታል ሬድዮ
Taem Radio
የሚጣፍጥ ታሪክ
ያ ስ ሙ
www.taem.et


ፀሐይ
አትጠልቅም
www.yederaw.com